የሰበር መ/ቁ. 33606

የካቲት 20 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሠ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች**፡- እነ አቶ ደጀኔ አበበ (5ሰዎች) - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጋቢት 4 ቀን 1999 ዓ.ም በእሸት የምግብ ውጤቶችና መኖ አክሲዮን ማህበር የዱቄት ፋብሪካ ላይ ቀደም ብሎ የተሰጠው እግድ መነሳት የለበትም በማለት የሰጠውን ትእዛዝ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ ማጽናቱን በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ይህን መሠረት በማድረግ ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች በእሸት የምግብ ውጤቶችና መኖ አክሲዮን ማህበር ላይ የሒሣብ ይጣራልን ክስ አቅርበው የዚሁ አክሲዮን ማህበር ንብረት የሆነው ዱቄት ፋብሪካ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ የሚል የዕግድ ትእዛዝ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አሰጥተዋል፡፡ በበኩላችን ደግሞ ፋብሪካው ለአክሲዮን ማህበሩ ለሰጠነው የብር 14,569,000(አስራ አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ስድሣ ዘጠኝ ሺ.ህ) ብድር በአንደኛ ደረጃ መያዣነት የያዝነው በመሆኑና ብድሩም እስካሁን ስላልተመለሰ ፋብሪካውን ሸጠን ገንዘባችንን ለማስመለስ እንድንችል እግዱ ይነሣልን በማለት ህዳር 12 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀናል፡፡



ሆኖም ጉዳዩን የያዘው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ህዳር 28 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሒሣብ ማጣራቱ ውጤት እስከሚታወቅበት ጊዜ ድረስ የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ የሚነሣበትን ሁኔታ ስላላገኘን አቤቱታውን አልተቀበልንም፣ እግዱ እንዳለ ይቀጥል ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ እንደገና ታህሣሥ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው እግድ እንዲነሣልን ብናመለክትም አሁንም ፍ/ቤቱ ራሴ የሰጠሁትን የዕግድ ትእዛዝ መልሼ የማነሣበት ምክንያት የለም በማለት ጥያቄያችንን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚሁ ጉዳይ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ብናቀርብም ይህ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤቱን ትእዛዝ በማፅናት ይግባኛችንን ሰርዞብናል፡፡

የሥር ፍ/ቤት ሒሣቡ እስኪጠራ ድረስ እግዱ አይነሣም ሲል የሰጠው ትእዛዝ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 የተሰጠውን ስልጣን እንዳይጠቀምበት ገደብ የሚጥል፣ መብት የሚነፍግ ከመሆኑም በላይ በአመልካች ባንክ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ነው ምክንያቱም የሒሣብ ማጣራቱ ሥራ እንደተመለከትነው የጊዜ ገደብ ያልተቀመጠለት በመሆኑና የብድሩ ገንዘብ ወለድ እየጨመረ የድርጅቱ ንብረትም እየተበላሸ በመሆኑ እግዱ ባለመነሣቱ ምክንያት የሚደርሰው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡

የአክሲዮን ማህበሩ ንብረት የሆነው ዱቄት ፋብሪካ የታገደው ለዕዳው ተጠያቂ በሆኑ የማህበሩ አባላት በሆኑት ሰዎች በነበረው የሒሣብ ክርክር መነሻነት ሲሆን ባንኩ የሚፈለገው ብር 22,000,000(ሃያ ሁለት ሚሊዮን) ደግሞ የማህበሩ አባላትና የአክሲዮን ማህበሩ የጋራ ዕዳ ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹ የሰጡት ትእዛዝ ደግሞ ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 98/90 የተሰጠውን በብድር የሰጠውን ገንዘብ የመሰብሰብ ሥልጣን የሚገደብና በሕዝብና መንግሥት ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ነው፡፡

በመሆኑም ሰበር ሰሚው ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ትዕዛዝ በመሻር እግዱ እንዲነሣ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎቹ (ፋብሪካው) ታህሣሥ 4 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ እሸጉ የምግብ ውጤቶችና መኖ አክሲዮን ማህበር ከአባላቱ መዋጮና

ከአመልካች ባንክ በተገኘው ብድር በብር 53,000,000 የተመሠረተ የዱቄት ፋብሪካ ነው፡፡ የአክሲዮን ማህበሩ ቦርድ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ለሶስት ተከታታይ ዓመታት አባላትን ባለመጥራቱና ሪፖርትም ባለማቅረቡ የተነሣ በስር ፍ/ቤት የሒሣብ ይጣራ ክስ ተመሥርቷል፡፡ ንብረቱ እንዳይባክን ፋብሪካው ሒሣቡ ተጣርቶ እስከሚያልቅ ጊዜ ድረስ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ባቀረብነው ጥያቄ መሠረት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ ተሰጥቶልናል፡፡ አመልካችም እግዱ እንዲነሣለት አመልክቶ በፍ/ቤቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በዚሁ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ማለት ሲገባው አመልካቹ እንደገና ተመሣሣይ የሆነ የእግድ ይነሣልኝ ጥያቄ መጀመሪያ የእግድ ትእዛዝ ለሰጠውና እግዱ እንዲነሣ ጥያቄ ቀርቦለትም እግዱ አይነሳም ላለው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ይህ ፍ/ቤት ራሱ የሰጠውን ትእዛዝ የሚያስለውጥ ሌላ ትእዛዝ መስጠት ስለማይችል የአግድ ይነሣልን ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው፡፡ ፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ መሠረዙ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

እኛ የእግድ ትእዛዝ እንዲሰጥልን ያመለከትነው የማጣራት ሥራው እስኪያልቅ ጊዜ ድረስ ፋብሪካው ካልታገደ የሒሣቡ ጉድለትና የንብረቱ መባከን ሣይታወቅ ተሸፋፍኖ ይቀራል የሚል ስጋት ስላደረብን ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹም የሰጡዋቸው ትእዛዞች ይህን ስጋት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

የማጣራት ሥራው በአፋጣኝ ሊከናወን ያልቻለው አመልካች የዱቄት ፋብሪካውን በሮች በመበየድ አጣሪዎች እንዳይገቡ በመከላከሉ መክንያት ነው፡፡ ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው ፍ/ቤት አመልካች ብይዱን እንዲያነሣና የሒሣብ ማጣራት ሥራው እንዲቀጥል ሲል ትእዛዝ የሰጠ ቢሆንም እስካሁን የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ተግባራዊ አልሆነም፡፡

በመሆኑም አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጀመሪያ እግዱ አይነሳም በማለት በሰጠው ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ማለት ሲገባው እንደገና የእግድ ይነሣልኝ ጥያቄ ማቅረቡ አግባብ ባለመሆኑና የሥር ፍ/ቤት ደግሞ ራሴ የሰጠሁትን ትእዛዝ መልሼ ራሴ ላነሣው አልችልም ያለው በአግባቡ በመሆኑ፣ ፌ/ከ/ፍ/ቤት



የሰጠው ትእዛዝም የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ በስር ፍ/ቤቶቹ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም፡፡ ሰበር ሰሚው ችሎትም ይህን ተመልክቶ በሥር ፍ/ቤቱቹ የተሰጡትን ትክዛዞች እንዲያፀናልን ሲሉ አመልክተዋል፡፡

አመልካችም የመልስ መልሱን በማቅረብ በአቤቱታው የተጠቀሱትን ክርክሮች ለማጠናከር ሞክሯል፡፡

በበኩላችን ደግሞ በአመልካቹ የቀረበውን የዕግድ ይነሣልኝ ጥያቄ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ የዱቄት ፋብሪካው የተመሠረተው ከአመልካች ባንክ በብድር በተገኘው ገንዘብ ጭምር መሆኑን ስላመኑና ለዚህ በብድር ለተገኘው ገንዘብም ፋብሪካው በአንደኛ መያዣነት አልተመዘገበም ብለው ስላልካዱ አመልካቹ ያቀረበው የእግድ ይነሣልኝ ጥያቄ በአግባቡ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የሥር ፍ/ቤቱ መጀመሪያ የሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ደግሞ በአክሲዮን ማህበሩ አባላት መካከል የሒሣብ ይጣራልን ክስ ቀርቦ በክርክር ላይ ባሉበት ጊዜ ከአባላቱ በአንዱ ወገን ሒሣቡ ሣይጣራ ፋብሪካ እንዳይሸጥ ለመከላል እንጂ በብድር ምክንያት በመያዣነት የያዘው ባንክ ገንዘቡን ለማስመለስ በማሰብ እንዳይሸጠው ለመከልከል እንዳልሆነ ከትዕዛዙ መንፈስ ለመረዳት ችለናል፡፡

አመልካች ባንክ በዋስትና የያዘውን ንብረት በመሸጥ በብድር የሰጠውን ገንዘብ ከነወለዱ የማስመለስ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት የተሰጠው በመሆኑ በዋስትና በያዘው ፋብሪካ ላይ የተሰጠው እግድ እንዲነሣለት ጥያቄ ማቅረቡ በአግባቡ ነው፡፡ ሆኖም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የእግድ ይነሣልኝ ጥያቄው ሲቀርብለት አመልካች በአዋጁ የተሰጠውን ሥልጣን መሠረት በማድረግ መብቱን ለማስጠበቅ እንዲችል የእግድ ትእዛዙን ሊያነሣለት ሲገባ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት መሆኑን ተመልክተናል፡፡

መጀመሪያ እግዱ አይነሣም የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶ እያለ በዚሁ ትእዛዝ ይግባኝ እንደማለት ተመልሶ እንደገና አመልካች ለዚሁ እግዱ አይነሣም